የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| ፱ኛ ዓመት ቁጥር ፯<br>9th year No 7 | | ሐረር መጋቢት ፱ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም<br>HARAR March 18th . 2005 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 1<br>Unit Price Br. 1 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት<br>ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.O.Box |


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር 50/1997 ዓ.ም

የታሪካዊ የጁገል ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ቅርስ ባለአደራ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 21/1992 ማሻሻያ አዋጅ---------------ገጽ 408


## አዋጅ ቁጥር 50/1997
## በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የታሪካዊ ጁገል ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ቅርስ ተንከባካቢ ባለአደራ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 21/1992ን ለማሻሻያ የወጣ አዋጅ

ታሪካዊው የጁገል ቅርስ በአለም አቀፍ ደረጃ ልዩ ትኩረት የተሰጠውና በዓለም ቅርስ መዝገብ ተመዝግቦ ተጨባጭ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያገኝ የጁገል ዙሪያ ጥብቅ መሬት (Buffer zone) በሰፋ መልኩ ግልጽ ተደርጎ የሕግ ከለላ እንዲያገኝ ማድረግ በማስፈለጉ፡-

የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የታሪካዊ ጁገል ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ቅርስ ተንከባካቢ ባለአደራ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 21/1992 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 50/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ማሻሻያ

የክልሉ መንግስት የታሪካዊ ጁገል ተንቀሳቃሽ ቅርስ ተንከባካቢ ባለአደራ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 21/1992 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ /1/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ አንድ ተተክቷል፡፡

"/1/ " የጁገል ክፍለ ከተማ " ማለት በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ ከተማ 3342 ሜትር ርዝማኔ ባለው አጥር ተከልላ በ48 ሄክታር የመሬት ስፋት የተቀረቀረችው ጥንታዊ የሐረር ከተማ አምብርት ክፍለ ከተማ እና ከግንቡ ውጭ በሰሜን መቀራዕ ወንዝን ተከትሎ በሰሜን ምስራቅ ሸንኮር ወንዝን ይዞ እስከ አው-ሹመር ወንዝ፤ በምሥራቅ በአው-ሹመር እስከ ማዊር ድረስ ሲሆን በምዕራብ በኩል ደግሞ ከዱከ በር አካባቢ ሁለቱን የመስተዳድር እና ማዘጋጃ ቤት ሕንጻዎችን አካቶ ወደ አስማዕዲን በሩ በመውረድ የአው-መሸሐድ /አይኮኮሄ ዋሻ/ መንገድን ተከትሎ የጅጅጋ መንገድን በመያዝ እና በመታጠፍ ከማዊር ወንዝ ጋር የሚገናኝ ቦታ ድረስ ያለውን ጥብቅ መሬት ያጠቃልላል፡፡

### 3. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምር የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር መጋቢት 9 ቀን 1997ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት